# የአቶ ለማ መገርሳ ተሞክሮ

[በወንድወሰን ተክሉ ፡ ጋዜጠኛ]

**መነሻ ጭብጥ-


አቶ ለማ መገርሳ

በሃያስድስት ዓመታት የህወሃት መራሹ አገዛዝ ውስጥ ያልታየና ያልተስተዋል ፖለቲካዊ እርምጃዎች ላለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የታየ ቢሆንም  እነ አቶ ለማ መገርሳና ቡድናቸው ወደ ስልጣን ከመጣበት ግዜ ጀምሮ የተወሰዱትና እየተወሰዱ ያሉት እርምጃዎች ግን የስርዓቱን መሰረት በፈነቃቀለ መልኩ ከስሩ ያናጋ፣ውስጡንም ያናወጠና ብሎም እያናከሰ ያለ ለየት ያለ እርምጃ ሆኖ ተገኝታል፡፡

በምስራቅ ኢትዮጵያ ኦሮሚያ ክልል ውስጥ የመንግስትን መዋቅር እንዳፈራረሰና መንግስታዊ ስራን ለመፈጸም አዳጋች አድርጓል እየተባለ ያለውን ቄሮ የተባለ ቡድንን የፌዳራሉ ፖሊስ ጥልቅ ምርመራ ማኳሄድ ጀምራል የሚለው የፖሊስ ኮሚሽነሩን አቶ አሰፋ አቢዩ መግለጫ ተሰምቶም ሳያበቃ የኦሮሚያ ክልሉ ፍትህ ቢሮ ሃላፊ አቶ ታዬ ደንደአ “የለም የክልላችንን ፀጥታ የሚመለከተው የኦሮሚያ ፖሊስ እንጂ የፌዴራሉ ፖሊስ ስራ አይደለም” በማለት ጉዳዩን ያጣጣሉ ሲሆን “ድርጊቱ ከሆነም” አሉ ባለስልጣኑ “ህገ ወጥ ድርጊት ነው” በማለት የፌዴራሉ መንግስት ያለኦሮሚያ መስተዳድር እውቅና እንዳሻው ጥልቅ ማለት አይችልም ሲሉ ይደመጣሉ።

ይህ በየክልሎቹ የፈላጭ ቆራጭነትን ስልጣን ያለተቀናቃኝ ሲጠቀም ለነበረው ህወሃት “በመቃብሬ” ላይ ከሚላቸው ህልውናውን እና ስልጣኑን ፈታኝ ክስተት በመሆኑ ብዙዎችን አጃኢብ አሰኝታል፡፡

በአምቦ እስከ አስር የሚደረሱ የመከላከያ ሰራዊት አባላት በታህሳስ ወር ውስጥ ተገድለዋል። በኦሮሚያ ክልል በፀረ ህዝብ ተግባር ላይ ተሰማርተው የተገኙ ሌሎች የሰራዊቱ አባላት በኦሮሚያ ክልል ፖሊስ ኃይል ታስረዋል። ዛሬ የኦህዴድ ባለስልጣናት ከፌዴራሉ መንግስት በተለይም ከህወሃት ባለስልጣናት የሚተላለፍን “ትእዛዝ አሻፈረኝ አንቀበልም” በማለት ካመፁ ሰነባብተዋል።

ከሁለት ወር በፊት በመከላከያ ምኒስትሩ አቶ ሲራጅ ፉርጌሳ እና በጠቅላይ ምኒስትሩ አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ በብሄራዊ ጸጥታ ምክርቤት የታወጀውን የአንድ አመት አስቸካይ ግዜ አዋጅን አፈር ከድሜ ያስጋጠው ይህው የኦህዴድ እምቢተኝነት ሲሆን የባህርዳሮቹም ብአዴኖች በተወሰነ ደረጃ ተሳታፊነት እንደሆነ እንረዳለን።

ህወሃት ለዓመታት በሞኖፖሊ ይዞት የነበረውን ስልጣን በእነ አቶ ለማ መገርሳ ግልጽና ይፋ ተቋውሞ [ቻሌንጅ] በድርጅታዊ ቀውስ ውስጥ ሊዘፈቅ ተገዷል፡፡

በዚህ ያልተጠበቀውና ለህወሃታዊያን ዱብ እዳ የሆነው አዲስ እርምጃና እምቢተኝነት መሪ ተዋናይ የሆኑት ደግሞ በህወሃቶች በኦሮሚያ የተቀጣጠለውን ህዝባዊ ዐመፅ ይቆጣጠራሉ ተብለው ወደ ስልጣን እንዲመጡ የተደረጉት እነ አቶ ለማ መገርሳ፣ዶ/ር አቢይ አህመድ፣አቶ አዲሱ አረጋና መሰሎቻቸው የመሆኑ ሁኔታ ብዙዎችን አስገርማል፣ብዙዎችን አጠራጥሮ እጅግ ብዙም አስብላል።

አንዳንዶች የእነ አቶ ለማ መገርሳን እርምጃ በህወሃት በጎፈቃድ የህወሃትን ስልጣን ካንዣበበት አደጋ እንዲታደጉ በሚል ወደ ስልጣን ከመጡ በሃላ  ሳይታወቅባቸው በህዝብ ድጋፍ ተበረታተው

ከመስመር የወጡ ሲሉ የሚገልጻቸው እንዳሉ የተስተዋለ ጉዳይ ሲሆን እነዚህ ወገኖች ዛሬ ዛሬ ይህን አባባላቸውን የዋጡት በመምሰል ዜማቸውን ቀይረው ሲናገሩ ይደመጣሉ፡፡

ኦህዴድና ህወሃት ከሚስማሙበት ይልቅ የሚፋለሙበት ክስተቶች እጅግ በርክተዋል፡፡ ከሁሉ በፊት ክህደቱ የተጀመረው በህወሃቶች በኩል እንጂ በኦህዴዶች በኩል እንዳልሆነ መረዳትም ያስፈልጋል፡፡ ህወሃቶች በጣም ታማኝ አገልጋያቸው በሆነው የኦህዴድ ድርጅት ላይ ክህደትን በመፈጸም ተሳልቀውባቸዋል፡፡

በምስራቅ ከሶማሌ ክልሉ አብዲ ኢሌ ጋር አብረው ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ የኦሮሞ ተወላጆችን ማባረርና ብዙዎችን መግደል ከክህደቶቹ ሁሉ የባሰው አስከፊ ክህደት በህወሃቶች በኩል በኦህዴዶች ላይ እንደተፈጸመ ይታወቃል፡፡

የምስራቁ ክስተት የአብዛኛውን የኦህዴድ ባለስልጣናትን ልብ በህወሃት ላይ ላይታረቅ እንዳሸፈተ ይነገራል፡፡ ይህን ክስተትም ፕሬዚዳንቱ አቶ ለማ መገርሳ በአግባቡ ሲጠቀሙበት እና ለህዝባቸውና ለሀገራቸውም በሚጠቅም መልኩ ለመጠቀም ስርዓቱን ከውስጥ ሆነው የፊጢኝ ሰንገው ይዘውታል፡፡

ለመሆኑ የአቶ ለማ መገርሳ አካሄድና አቋም፣ በተለይም ይዘው የተነሱት የኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ለፖለቲካዊ ትርፍ ታልሞ እየተቀነቀነ ያለ ስልታዊ ዜማ ነውን ወይንስ እውነተኛ የሆነ አቋም። ው

የአቶ ለማ መገርሳ አካሄድ ወደየት አቅጣጫ ሊያመራንስ ይችላል የሚሉትን ወሳኝ ጥያቄዎችን በማንሳት መልስ ፍለጋ ብንጋዝ የዛሬውንና ቀጣዩን መጪ ግዜን የምናይበትን እይታ ይፈጥራል ብዬ ስላመንኩ ቀጣዩን ጽሑፍ ላቀርብ ችያለሁ።

***የአቶ ለማ መገርሳና ህወሃት መሻኮቻና መተናነቂያ ህጋዊ ጭብጦች፡

ለአቶ ለማ መገርሳ፡ቡድናቸውና ብሎም ለአማራ ክልሎቹ እነ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው በኢህአዴግ ላይ ፊታቸውን ለማዞር የሚያስችሉ በርካታ ምክንያቶች/factors/ እንዳሉ ግልጽ ነው፡ የስርዓቱ አይዲኦሎጂ መንኮታኮት፡የፌዴራሉ መንግስት ህገ መንግስታዊ ስልጣን በክልል መንግስታት ውስጥ ሊፈጸም አለመቻል፡የህወሃት ተፍረክርኮና d, facto leader መሪ አልባ ሆኖ መገኘት እና ለዚህ ሁሉ መፍረክረክ ዋና ምንጭና መሰረት የሆነው በሁለቱ ክልሎች እና በተቀረውም የሀገሪቱ ክፍል የተነሳውና ወደ ሶስተኛ ዓመቱ የዘለቀው ህዝባዊው ዓመጽ እንደሆነ እንረዳለን፡፡

በምስራቅ ወለጋ ዞን በጉደያ ቢላ ወረዳ ተወላጅ የሆኑትና ከአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የመጀመሪያ ድግሪያቸውን በፖለቲካ ሳይንስ አግኝተው ማስተርሳቸውን በዓለም አቀፍ ግንኙት ያገኙት አቶ ለማ መገርሳ አስተውሎ ላደመጣቸው እነ አቶ ሙክታርና ወ|ሮ አስቴርን ተክተው የኦሮሚያን ፕሬዝዳንትነት ስልጣን ከተቆናጠጡበት ግዜ ጀምሮ የሚናገራቸው መርህ ተኮር አቋማዊ መገለጫዎች ሁሉ የተነሱበትን እና እንደ መሪም የሚያምኑበትን መርህ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ቢሆንም ልዩነቱ ግን ያኔ ቃል እንጂ ተግባር አልጀመሩም ነበርና ሁላችንም በጠርጥር መንጥር መነፅር ልናያቸው ችለናል።

ዛሬ ሰውዬው እጅግ ፈታኝ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ሆነው እየወሰዷቸው ካለው እርምጃዎች ውስጥ በርካታው የግንባሩ አስኳል ለሆነው ህወሃት ታማኝ አገልጋይነታቸውን የሚያረጋግጥ ታዛዥነት ሳይሆን ከታዛዥነት መስመር ያፈነገጡ መሆናቸውን የሚገልፁ ወሳኝ እርምጃዎች እንደሆኑ እያስተዋልን ነው።

የሁለቱ ማለትም የኦህዴድ እና ህወሃት መቆራቆሻና እርሰበርስ መተናነቂያው መንስኤ ወደ ሶስተኛ ዓመቱ እየተጋዘ ካለው ህዝባዊው እምቢተኝነትና ዓመፅ ባሻገር ለፖለቲካ ሳይንስ ምሩቁ አቶ ለማ መገርሳ ኢህአዴግ የሚተዳደርበትን ሕገ መንግስት መሰረት አድርጎ ለመነሳትም ሆነ ተገቢውን ጥያቄ ለማቅረብ የሚያግድ እንዳልሆነ ዛሬ ከሚያደርጉት እርምጃና እንቅስቃሴ አንጻር መረዳት አያዳግትም።

ሆኖም ላለፉት ሃያስድስት ዓመታት ውስጥ ያልታየና ያልተከሰተ ባህል በመሆኑ ስልጣኑን እና ኢኮኖሚውን በሞኖፖሊ የተቆጣጠረው ህወሃት ብቻ ሳይሆን እኛም ጭምር ይህ የአቶ ለማ መገርሳ እምቢተኝነት እውነተኛ አይደለም በማለት ትንቅንቃቸውን ለማጣጣል የተሞከረበት ወቅት ብዙም የራቀ አልሆነም፡፡

በመሰረቱ የአቶ ለማ መገርሳና ቡድናቸው ለእኛም ሆነ ለህወሃት እንግዳ መሰል ዱብ እዳ የመሰለን እምቢተኝነት የአራቱ ድርጅቶች [ኢህአዴግ] መተዳደሪያና የሀገሪቷ የበላይ ሕግ እንደሆነ በታወጀው ሕገ መንግስት መሰረት አግባብነት ያለው ብቻ ሳይሆን እስከዛሬ ድረስ የነበሩት የኦህዴድ ባለስልጣናት ለምን እንዳልተጠቀሙበት ጥያቄ የሚያስነሳ እንጂ አቶ ለማን የሚያስጠቃ እንዳልሆነ ህግ ተብዬው ይገልጻል። ግን ህግ በሀገራችን የእኔ እና የእናንተ መቀጫ፣ መታገጂያና መወገዣ እንጂ የህወሃታዊያን መዳኛ እንዳልሆነ እናውቃለን፡፡

የቱንም ያህል በህወሃታዊያን ዘንድ አንደ ክህደትና አልታዘዝም ባይነት ቢታዩም አቶ ለማ መገርሳና ቡድናቸው እስካሁን ድረስ እየወሰዱት ያለው እርምጃ ሁሉ ህገ መንግስቱ ላይ በሰፈረው የክልል መንግስታት ፕሬዚዳንቶች ስልጣን እና የየክልሎቹ ህገ መንግስታዊ ስልጣን መሰረት እንደሆነ ማንኛችንም ብንሆንም ልንስተው አይገባም።

ለዚህ ለአቶ ለማ መገርሳና ቡድናቸው አዲስ እርምጃና አቋም እንግዳና ያልተጠበቀ እርምጃ እንደሆነ እድናስብና ብሎም አምነን እንድንጠራጠርም ሆነ እንድንደነቅ ያደረገን የስርዓቱ ላለፉት ሃያስድስት ዓመታት አገዛዛዊ ስልትና ሁኔታ እኛም ክስተቶችን ስርዓቱ ባዐደቀውና በሚገዛበት ህገ መንግስት መመርመሪያ ማየቱን በመተው በተለምዶና በዘልማድ በታወቀው የህወሃት የበላይነት አገዛዝ ስለምንለካው የእነ አቶ ለማና ቡድናቸው ህገ መንግስቱን የተከተለው እርምጃን ከህወሃታዊያን ባልተናነሰ መልኩ በእንዴት ሊሆን ቻለ አግራሞትና ጥርጣሬ ለማየት የተገደድነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ብዣሃነትን ያቀፈ መንግስርታዊ ይዘት ለማቋቋም ሲባል በአንድ ሀገር ውስጥ ሁለት መንግስታትን በፌዴራልና በክልል መንግስታት ተብለው በሚጠሩ መንግስታዊ አወቃቀር እንደተዋቀረ በተነገረን ህገ መንግስት መሰረት ዘጠኙ የክልል መንግስታትና ፕሬዚዳንቶቻቸው የሚጠቀሙትን ስልጣን በግልጽ ለይቶ እንዳስቀመጠ ግልጽ ነው።

በህገ መንግስቱ የስልጣን አወቃቀር መሰረት ዛሬ በኦህዴድና በብአዴን በኩል የቀረቡት “ የመብታችን ይከበር” ጥያቄና “የእንደ እምንወክለው ህዝብና ቆዳ ስፋት በፌዴራሉ መንግስት ውስጥ ሚና ይኑረን” ጥያቄ ህገ መንግስታዊ መሰረት ያለው ፍትሃዊ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን እንዴት እስከዛሬ ድረስ በኦሮሚያ ያለፉት ስድስት ፕሬዚዳንቶችና በአማራ አስተዳድረው ያለፉት ሶስት ፕሬዚዳንቶች ይህንን ጥያቄ ሳያነሱ እና ለተፈጻሚነቱም ሳይታገሉ ቀሩ የሚያስብል እንደሆነ ነው መረዳት የሚቻለው።

አቶ ለማ መገርሳና ቡድናቸው ከእነሱ በፊት የኦሮሚያን ግዛት ለህወሃት ፈረስ ሆነው በመጋለብ የኦሮሞን ህዝብ በልተው ካስበሉት ስድስት ፕሬዚዳቶች [ሀሰን አሊ፣ኩማ ደመቅሳ፣ጁነዲን ሳዶ፤ አባዱላ ገመዳ፣አለማየሁ አቶምሳ እና ሙክታር] በተለየ ሁኔታ በህገ መንግስቱ ላይ የሰፈረውን

ክልላዊ ስልጣን ለመጠቀምና ብሎም ለማስከበር የተነሱበት ምክንያት ህግ የማያውቀውንና የማያከብረውን ህወሃት ህገ መንግስቱን ያከብራል በሚል የዋህነት ሳይሆን በስድስቱ ቀደምት የኦሮሚያ ፕሬዚድንቶች ወቅት ከቶም ቢሆን ያልታየውና ያልተከሰተው ህዝባዊው ዓመፅ ምክንያት እንደሆነ ከበቂ በላይ መግለፅ ይቻላል።

በኦሮሚያ፣በአማራና በተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች የተቀጣጠለው ህዝባዊው ዓመፅ በትምህርት ለበሰሉት እንደነ አቶ ለማ መገርሳና ቡድናቸው በህዝባዊው ኃይል እንዲተማመኑ ብቻ ሳይሆን የህዝባዊውን ጥያቄ በአግባቡ እንዲመልሱ በማስጨነቅ መፍትሔ ፍለጋ እንዲባዝኑም እንዳደረጋቸው ይታመናል።

የፌዴራሉ ስልጣን እና ኢኮኖሚ አከፋፈል እንደየክልሎቹ ህዝብ ብዛት ላይ ተመርኩዞ ይሆናል የሚለው ህገ መንግስታዊ የስልጣንና የኢኮኖሚ አከፋፈል ያልተጻፈ ያህል ላለፉት ሃያስድስት አመታት በህወሃት የበላይነት ሲካሄድ የነበረው አገዛዝ ለህዝባዊው ዓመጽና ለሀገሪታም በአስጊ ሁኔታ ላይ እንድትገኝ ማድረጉን በየእለቱ ከሚታየው ህዝባዊ ዓመጽ መፈክሮችና ጥያቄዎች ማወቅ ይቻላል።

ህገ መንግስቱ ላይ የሰፈረውን የክልሎችን ስልጣን እና መብት ማስከበር ከቻሉ በኦሮሚያም ሆነ በአማራው ክልል የተነሳውን ህዝባዊ ጥያቄ መመለስ መቻላቸው ብቻ ሳይሆን በአንፃሩና ጎን ለጎን እራስን በራስ የማስተዳደሩ ጉዳይን፤ ማለትም ያለምንም ጣልቃ ገብነት የመተግበሩን አስፈላጊነትና ወቅታዊነትን አምነው ለማስፈጸም እንደተነሱ ከተግባራቸውና እቅዳቸው መናገር ይቻላል።

የእነ አቶ ለማ መገርሳ እርምጃና አቋም ህገ መንግስታዊ ገደቡን ያከበረና እንዲያውም ለህገ መንግስታዊ ተፈጻሚነት የቆመ ሆኖ ሳለ በህወሃታዊያን ዘንድ የትኛውም ህገ መንግስቱን መሰረት ያደረገው ህዝባዊ ጥያቄም ሆነ የየክልሎቹ ፕሬዚዳንቶች ጥያቄ ተቀባይነትን የማያገኝና ብሎም ጥያቄውን በሚያነሱት ላይ ጦርነት የሚያሳውጅ በመሆኑ እዚህጋ የህጋዊነትና የህግ አፍራሽነት ጉዳይ ከግንዛቤ እንዳይገባ በማድረግ የመደፍጠጥ ፍላጎትና አላማ ነው ሂደቱን ውስብስብ ሊያደርገው የቻለው።

ህገ ንመንግስታዊው ደንብ ተከበረ ማለት ላለፉት ሃያስድስት አመታት በበላይነት ያሻውን በመዝረፍ፣ያሻውን በመግደልና በማሰውር ስልጣንን እና ኢኮኖሚውን የተቆጣጠረው ህወሃት ሁሉ ነገሩ አከተሞ እሱም በቁመትና ወርዱ ሊስተናገድ ይገደዳል ማለት ነው።።ህገ መንግስቱ የአሃዳዊዉን ማእከላዊ መንግስትን ስልጣን ወደ ክልሎች እንዳከፋፈለ [devolve] እንዳደረገ ተቀምጧል፡፡ በዚህ ስልጣንን ባከፋፈለው /power devolution /ህግ መሰረት ክልሎች እስከዛሬ ድረስ ያልተጠቀሙበትና ሊጠቀሙበትም ያልቻሉት ስልጣን እንዳላቸው ስንረዳ የአቶ ለማ መገርሳ እና ቡድናቸው አካሄድ በሙሉ እራሳቸው ህወሃቶች ባጸደቁት ህግ መሰረት እንደሆነ መረዳት አያዳግትም፡፡

የአለም አቀፉን ማህበረሰብና የዋህ ኢትዮድያዊያንን ለማታለል ሲል ጥምር የፖለቲካ ስርአትን ያቀፈ የፌዴራል ስርአት ያወጀው ህወሃት በታሪኩ ተግብሮትና ተጠቅሞበት የማያውቀውን ህግ [የህወሃትን ጥቅም በሚያስጠብቅ ደረጃ ህገ መንግስቱን አክባሪ ሆኖ ሲቀርብ ድርጅታዊ ጥቅሙን በሚነካበትና በሚጎዳበት ማንኛውም ሁኔታ ላይ ግን ህገ መንግስቱን አፍራሽ በመሆን እየገዛ ያለ ስርአት ነው] መንግስት ዛሬ በዚህ ሁኔታ ላይ በፍጡራኖቹ ቁጥጥር አክባሪ ሆኜ እቀጥላለሁ ይላል ብዬ አልጠብቅም።

ህወሃት የህገመንግስቱ አክባሪ ሆኖ የፌዴራሉን ክልላዊ መንግስት ስልጣንና የኢኮኖሚ አከፋፈል እንደ ህጉ መሰረት በክልሎቹ ወርድና ቁመና መሰረት በማድረግ ከእነ አቶ ለማ መገርሳና አቶ ገዱ አንዳርጋቸው የተሰነዘረበትን ፈታኝ ሁኔታን ይፍርታል ብዬ ለመገመት የሚያስችሉኝ

የህወሃት የሃላ ታሪክ ድጋፍ ስለሌለ ይህንን የስልጣን መፈታተንን ሁኔታ በመጀመሪያ በሚያዘናጋ ተስማሚነት መሳይ ግዜ ከገዛ በሃላ አሁን ውስጥ ለውስጥ እያካሄደ ያለውን እነዚህን ሰዎች የመተካቱ ሁኔታን ካሳካ የሃይል እርምጃን በመጠቀም ጨፍልቆ የቆመለትን በህወሃት የበላይነት ስር የሚሾር ኢህአዴግን እንደሚፈጥር ከግምት በላይ መግለጽ ይቻላል።

ይህን ስል ህወሃት እነ አቶ ለማ መገርሳን፣እነ አቶ ገዱ አንዳርጋቸውን ጨፍልቆና ድጦ የበላይነቱን በመቀዳጀት ሀገሪታን መግዛት ይቀጥላል ማለት ሳይሆን ድርጅቱ አሁን የቀረበለትን ስልጣኑን ፈታኝ ሁኔታን ቢሳካለትም ባይሳካለትም እንደመፍትሔነት አምኖበት የሚወስዳቸው እርምጃዎች ናቸው ማለቴ እንጂ ለአሸናፊነቱ ወሳኙ የሰፊው ህዝብ ትግሎ ብቻ እንደሆነ መረዳት ተስኖኝ አይደለም።

ሆኖም አቶ ለመገርሳን ፈረንጆች እንደሚሉት The right person at the right time በማለት የሚገልጿቸው ወገኖች በጣም በርክተዋል፡፡ የእነዚህ ሰዎች ቁጥር መበራከት ሰውዬ እያስተጋቡና እየተገበሩት ኢትዮጵያዊነት አቋም ምክንያት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት እና ህልውና በህወሃት በጎፈቃድ የተጠበቀ ይመስል እራሱን በሚያመጻድቀው ህወሃቱ ሊ/ር ደብረጺዮን ፊትለፊት "ኢትዮጵያ እንደገበያ ማንም ሲሻው የሚሰበስባትና ሲሻው የሚበትናት ሀገር ሳትሆን እጅግ ረቂቅ የሆነችና ማንም የማይገልጻት ታላቅ ሀገር ነች" ሲሉ አቶ ለማ መገርሳ በግልጽ ሲናገሩ የመጀመሪያቸው ሳይሆን በተግባርም የተፈጸመ እውነተኛ የኢትዮጵያዊ ብሄረተኝት አቋማቸው እንደሆነ እያየን ነው፡፡

***የአቶ ለማ መገርሳ ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ስልታዊ ወይንስ መሰረታዊ የአቋም መገለጫ፥

ባለፈው ሳምንት የተላለፈውን የአራቱን የድርጅት መሪዎች መግለጫን እንደ እኔ የተከታተለው አንድ ወዳጄ “ኦህዴድ አምጣ አምጣ ስድስት ሴቶችን ከወለደች በሃላ በስንት ስለት ሰባተኛውን እውነተኛ ወንድ ልጅ ወልዳለች” ሲል የአቶ ለማ መገርሳን ሰባተኛ የኦሮሚያ ፕሬዚዳንትነትን ካለፉዋቸው ስድስቱ ፕሬዚዳንቶች ጋር በማነጻጸር ስድስቱን እንደ እንስቶች [እዚህጋ እንስቶችን ከአቅመቢስነት ጋር ለመግለጽ ሳይሆን በኦሮሞ ባህል ዘንድ የቤተሰብ መሪ ሆኖ በታላቅነት ወንድ መወለድ አለበት ፤ ወንዱም ነው የገዳን ስርአት ተቀብሎ በአባት ምትክ የሚፈጽም በመሆኑ የቀረበ ተምሳሌት እንጂ ከውድ እንስት እህቶቼ ጸታና አቅም አንጻር እንዳልቀረበ እንድትረዱልኝ ከወዲሁ ላስገነዝብ እወዳለሁ] በመቁጠር ኦሮሚያ አሁን ገና የምትፈልገውን ወንድ መሪ ወለደች ሲል ተናገረ።

የአራቱን መሪዎች በወቅቱ የሀገራችን ጉዳይ ላይ ድርጅታቸው ኢህአዴግ ያለውን መረዳትና እይታ ሲገልጹ የአቶ ለማ መገርሳ መልስ በብዙ ሚሊዮኖች ልብ ውስጥ ሁነኛ ስፍራ እንዳገኘ ለማወቅ አዳጋች አልሆነም።

ሰውዬው ከኦሮሚያ ፕሬዚዳንትነት ባሻገር የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ተብነው በነጻው ማህበራዊ ድረ ገጽ ሚዲያ ላይ ያስመረጣቸውን ኢትዮጵያዊነትን እና ብሎም ኢትዮጵያን የመምራት ብቃትን ያንጸባረቁበት ክስተት ሆኖ በብዙዎች ታይታል።

ዛሬ ሀገሪቷን እየገዛ ካለው ጥምሩ ግንባር ኢህአዴግ ውስጥ በሃገራዊ ሃላፊነት፣በሃገራዊ ራእይ፣ ተቆርቋሪነትና በአፍቃሬ ኢትዮጵያዊነቱ የተነሳ አቶ ለማ መገርሳ በስርአቱ ውስጥ የተገኘ በቻኛ ሰው መሆኑን ብዙዎች ሲናገሩ መስማትም ሆነ ማንበብ ተችላል። በእርግጥም የሀገራችንን ወቅታዊ ችግሮችን ከእነ መንስኤያቸውና መፍትሄያቸው ከመመለስ አካያ አቶ ለማ በእለቱ ከጎኑ ከተደረደሩት ሶስት የገደል ማሚቶዎች ልቀውና ረዝመው ሲታዩ ሶስቱ ደግሞ ይበልጥ ድንክ እንዳደረጋቸው ማየት ተችላል።

የአቶ ለማ መገርሳን ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነትና ሀገራዊ አቋም ከኦህዴድ ነባራዊ ታሪክና ልምድ በመነሳት ለፖለቲካዊ ትርፍ ሲባል የተደረገ ስልት ነው የሚሉ ወገኖችን አንሰማለን። የእነዙህን መሰል ወገኖች ድምጽ ከአንድ አመት በፊት በስፋት ስንሰማውና አንዳንዶቻችንም መልሰን ይበልጥ ያስተጋባነው ጥርጣሬ ወለድ አመለካከት ሲሆን በወቅቱ ግን በትግባር ያልተፈተነ ከመሆኑ አንጻር ተከላካይም ሊገኝለት እንዳልቻለ የምናስታውሰው ይመስለኛል።

የጣናን ኬኛ መፈክርን አንግቦ ወደ ባህር ዳርና ጎንደር የተመመው ከሁለት መቶ በላይ የኦሮሞ ወጣት እርምጃ በእነ አቶ ለማ መገርሳ፣አቶ አዲሱ አረጋና ዶ/|ር አቢይ አህመድ ትእዛዝና ድጋፍ ባይሆን ኖሮ መቼም ሁላችንም እንደምናውቀው ይህ  ስልጣን አልባ  የሆነው ወጣት ዝም ብሎ በራሱ ግዜ ብድግ ብሎ ከአምስት በላይ አውቶቢስና ሌሎች መኪኖችን አንቀሳቅሶ  ወደ ባህርዳር መሄድ ቻለ  ብለን አናስብም።

የኦሮሚያ ወጣቶችን በጣናን ኬኛ መፈክር ወደ ባህርዳር ሲሰድ እንዲንሸራሸሩ ነውን ወይንስ ምን ፈልጋ ነው?በእርግጥ እምባጭ የተባለውንና የጣናን ሓይቅ ውሃ በማትነን ለሓይቁ ከፍተኛ አደጋ የሆነውን አረም ለመንቀል ቢሆንም የአዲስ አበባ ከተማን ስፋት የሚያህል የሸፈነውን አረም በአንድ ቀን ዘመቻ ለመንቀል ቀርቶ ለወራትና ለአመታትም ባለመቻሉ እነሆ ማሽን እየተፈለገለት እንደሆነ እናውቃለን።

የኦሮሚያ ቄሮዎች በእነ አቶ ለማ መገርሳና ቡድናቸው ድጋፍ ብቻ ሳይሆን ትእዛዝ ጭምር ወደ ባህርዳር እንዲጋዙና በሁለቱ ህዝቦች መካከል በህወሃት የተዘራውን ልዩነትና ጥላቻ እንዲነቅሉ በመታዘዝ የፈጸሙ ሲሆን ይህ ደግሞ ከወራት ቆይታ በሃላ በአጠቃላይ በአቶ ለማ መገርሳ መሪነት የኦሮሚያ ክልል ባለስልጣናት፤አባገዳዎች፣አርቲስቶች፣ምሁራን፣ወጣቶችና አመራሮች በአየርና በየብስ ወደ ባህርዳር ተጉዘው ታሪካዊውን የህዝብ ለህዝብ ግንኙነትን ስራ በስኬታማነት መልኩ እንዲሰሩ እንዳስቻላቸው ይታወሳል።

እነ አቶ ለማ መገርሳ ባህርዳር ድረስ ለምን ተጋዙ?ለታይታ ፖለቲካ ነው?የአቶ ለማ መገርሳ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት ዛሬ የተጀመረ ሳይሆን ቀደም ብሎም የነበረ ግናስ ከነበረበት አከባቢ አካያ እያታ ያላገኘ ሲሆን ሰውዬው ከኦሮሚያ ተሻግሮ እራሱን በኢትዮጵያ ደረጃ በማስቀመጥ ሰፊው የኦሮሞ ህዝብ እንደ ብዙሃንነቱ በሀገሪቱ ውስጥ ሊጫወት የሚፈልገውን የአንበሳውን ድርሻ ለመጫወት በኢትዮጵያ ብህሄርተኝነት ብቻ እንደሆነ በመረዳት እያንፀባረቀ ያለ እውነተኛ አቋሙ እንደሆነ ከግምት በዘለለ መልክ እመለከተዋለሁ።

ለአቶ ለማ መገርሳ ኢትዮድያዊ ብሄርተኝነት ማስረጃህ ምንድነው ለምትሉኝ ማስረጃዎቼ የሰውዬው አንደበት ብቻ ሳይሆን ተግባራቶቹ ከሁሉም በላይ ማስረጃዎች ሲሆኑ በእስካሁኑ የአንድ አመት ከመንፈቅ በኦሮሚያ ፕሬዚዳንትነቱ ከተናገራቸው ይልቅ እያደረጋቸው ባሉት ተግባራቶቹ ላይ ስናነጣጥር ጎልቶ የሚታየን የአቶ ለማ መገርሳን ድንቅ ኢትዮድያዊ ብሄርተኝነቱ እውነተኛ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ ለጊዜያዊ ፖለቲካዊ ጥቅም ስሌት ብሎ እጅግ በርካታና ድንቅ ግን ስልጣኑን እና ህይወቱን ለአደጋ የሚያጋልጥን ተግባር መፈፀም ይቻለዋል ብዬ መቀበሉ የሚቻለኝ ስላልሆነ ነው።

ከኢትዮጵያም አልፎ በአፍሪካ ቀንድ በህዝብ ብዛቱና በቆዳ ስፋቱም አንደኛ የሆነውን የኦሮሞን ህዝብ የሚወክለው ፕሬዚዳንት ለማ መገርሳ ይህን ታላቅ ህዝብ ይዞ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነትን ማራመድ ማለት በእርግጥም እንደግለሰብ ለራሱም እንደ የኦሮሞ ህዝብ መሪም ለኦሮሞ ህዝብ እና የኦሮሞ ህዝብ ለሚኖርበት ሀገር ኢትዮጵያ ታላቅ ትርፍና ጠቀሜታን እንደሚጎናፀፍ አቶ ለማ መረዳት የሚያቅተው ነው ብለው የሚያስቡ ብቻ ዛሬ የምናየውን ኢትዮድያዊ ብሄርተኝነትን በጥርጣሬ ሊያዩ ይችላሉ።

በኦሮሚያ ክልል ያለውን የኦሮሞ ብሄርተኝነትን ወደ ኢትዮጵያ ብሄርተኝነት በመለወጥ ይህ ታላቅ ህዝብ ይገባኛል ያሚለውን መብቶቹን በኢትዮጵያዊነቱ ተከብሮለት እንዲጫወት ለማድረግ ከፍተኛ ሀገራዊ ሃላፊነትን እና ሀገራዊ ራእይምንም ጭምር ሰንቆ የተገኘም መስሎኛል የአቶ ለማ መገርሳ በዚህች እጅግ ውጥንቅጡ በወጣባት የሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ ብቅ ማለት የተለየ ተልእኮና አላማም አንግቦ እንደተነሳ መሪ አድትርጌው እንዳየው የሚያደርጉኝ ብዙ የእይታ አቅጣጫዎች ቢኖሩኝም  በዋነኝነት ግን ከላይ ያሰፈርካቸው ተጠቃሽ ክስተቶች ናቸውና የዚህን ሰውዬ አካሄድና ግብግብ ሙሉ በሙሉ የሁለንተናዊው የነጻነት ትግሉ መሪ ሃዋሪያ ነው የሚያስብለኝ ባይሆንም ግን የህወሃትን የተንዛዛና የጠነዛውን የበላይነትን አገዛዝ በመገርሰስ በኩል የሚጫወተው ሚና አጅግ ከፍተኛ በመሆኑ ማንኛችንም በቅርበትና በአትኩሮት ልንከትልና ልንረዳው የሚገባን ሰው ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

ሆኖም አቶ ለማ መገርሳ ከተጋፈጠው አደገኛ ባላንጧ አቅምና ጉልበት አንጻር መክቶ ለማሸነፍ የተቀረውን ህዝብ ድጋፍ ማስፈለጉን የተረዳ ሰው ብቻ ሳይሆን እወክለዋለሁ ባለው የኦሮሞ ህዝብ ወርድና ቁመት አኳያ በኢትዮጵያ  ውስጥ ለመጫወት የሚቻለው በኢትዮጵያ ደረጃ ዓላማና አቋምን በመያዝ ብቻ እንደሆነ ከመረዳትም አልፎ  ያመነበትም ይመስለኛል ከአጠቃላይ እንቅስቃሴው በመነሳት፡፡

ያ ማለት አቶ  ለማ መገርሳና  ድርጅታቸው ከኦሮሚያ ባሻገር ያለሙና አቅምም ያላቸው መሆናቸውን እያሳዩን ሲሆን በህወሃት በኩል ይህንን አደጋ ለመከላከል በፖለቲካ አመራር ብቃቱ የተንኮታኮተ ስለሆነ  ወታደራዊውን ሃይል በመጠቀም ለማፈን እና የክልሎችን ስልጣን ለመግፈፍ እንደሚንቀሳቀስ ይጠበቃል፡፡

በእርግጥ በአሁኑ ሰዓት በትግራይ መቀሌ ስብሰባ ላይ ያለው ህወሃት እያወጣ ካለው መግለጫ መረዳት የምንችለው ድርጅቱ የክልሎችን ስልጣን በመገደብና በመቆጣጠር እነ አቶ ለማ መገርሳን ለማሽመድመድ እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ  እያየን ነው፡፡

ህወሃት ሰሞኑን እያወጣ ካለው የጸጥታ  ችግሮች መግለጫ ድርጅቱ እነ አቶ ለማ መገርሳን ስልጣን ለማሳጣት በከፍተኛ ሁኔታ  እየተንቀሳቀሰ ሲሆን አጠቃላይ የጸጥታ ማስከበሩን ጉዳይ በፌዴራል ስም ለመጠቅለል ዓላማን ይዞ  እየተንቀሳቀሰ ነው።

በእነ አቶ ለማ መገርሳ በኩል ይህን የህወሃት አካሄድ የተቀበሉ ሳይሆን ከዚህ በፊት በነበረው አካሄድ እንኳን የህወሃት ፈረስ ሆነው ላለመቀጠል የወሰኑና ካድሬያቸውንም ያዘጋጁ በመሆናቸው ህዝባዊው ትግልና  ድርጅታዊው ግብግብም በወሳኝ ምእራፍ ላይ እንዳለ ድርጊቶቹ ከበቂ በላይ በሆነ ሁኔታ እያሳዩን ነውና ለሁለን ተናዊው ድል ወሳኙን ትግል ማጧጧፍ የሚገባን ወቅት እንደሆነ  ነው መረዳት የምችለው፡፡

በቀጣዩ መጣጥፌ በአፍሪካ ቀንድ ዙሪያ ፡ በግብጽ፡ሱዳን፡ኤርትራና ቱርክ መካከል እየተካሄደ ያለውን ሁኔታ የምንቃኝበትን ይዤ እስክቀርብ ቸር እንሰንብት!

------------------------------------------------------------------------------------------

ላለፉት ጽሁፎቼ የተለያየ አስተያየታችሁን በግል ኢሜይል ለላካችሁልኝ አንባቢዎች ልባዊ ምስጋናዬን እያቀረብኩ ዛሬም ጥያቄና አስተያየታችሁን በኢትዮሚዲያ ኢሜይል በኩል ወይም በግሌ teklu7@gmail.com ብላችሁ ብትልኩልኝ ከምስጋና ጋር እመልሳለሁ